# ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያንጉዙ
# የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ
# ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ
# አፈፃፀም የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 13/2001

ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተደረገባቸው እና የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመባቸውን ህገ-ወጥ እቃዎች በሚያጓጉዙ ማጓጓዣዎች ላይ በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት ሊወሰድ የሚገባውን አስተዳደራዊ እርምጃ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የማጓጓዣ ባለቤቶች በንብረታቸው አማካኝነት ለሚፈፀም ህገ-ወጥ ድርጊት ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ በንብረታቸው ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ እንዲችሉ ወጥነት ያለው መስፈርት ማውጣትና ለጉዳዮች እልባት መስጠቱ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ሕገወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ ማጓጓዣዎች ባለቤት ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 13/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፦

1) "ማጓጓዣ" ማለት እቃዎችንና ሰዎችን የሚያጓጉዝ ማንኛውም የማጓጓዣ ዘዴ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል።
2) "ሕገ ወጥ እቃ" ማለት በባለስልጣኑና ባለስልጣኑ በሚያስፈጽማቸው ሕጎች የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት እቃ ነው።
3) "ባለቤት" ማለት ማጓጓዣውን የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማስተላለፍና የመጠቀም መብት ያለው ሰው ሲሆን የጋራ ባለመብቶችንም ይጨምራል።
4) "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት ባለቤትነት የሚተዳደር መሥሪያ ቤት ነው።
5) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው።
6) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ህገ-ወጥ እቃዎችን የሚያጓጉዙ ማጓጓዣዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ውለው ውሣኔ እስኪሰጥባቸው ድረስ ለሕገ ወጡ ድርጊት ባእድ የሆኑ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ሊደርስ የሚችልን እንግልት እንዲሁም ተሽከርካሪው በቁጥጥር ሥር ሲውል ሊከሰት የሚችልን ተጨማሪ ኪሳራ በማስወገድ ለጉዳዮች አፋጣኝ አስተዳደራዊ ውሣኔ ለመስጠት እንዲቻልና ተሽከርካሪው በተመሳሳይ ህገ-ወጥ ድርጊት ላይ ተሳታፊ ያለመሆኑን ማረጋገጥ ነው።

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ማጓጓዣውን ሲያሽከረክር የነበረው የማጓጓዣ ኃላፊ የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 61(2) መሠረት በዋስትና በሚለቀቁ ማጓጓዣዎችና በመንግስት መሠሪያ ቤት ተሽከርካሪዎች ላይ በስተቀር በማናቸውም ማጓጓዣዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

# በአስተዳደራዊ ውሣኔ ስለመጨረስ

## 5. ስለማመልከቻ አቀራረብ

የማጓጓዣው ባለቤት የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ከራሱ እውቅና ወይም ፈቃድ ውጪ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን በማያያዝ ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲያልቅለት ማጓጓዣው በቁጥጥር ሥር በዋለ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለሚገኘው የምርመራ ቡድን ካላመለከተ ጉዳዩ በሕግ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

## 6. ማመልከቻን ስለመመርመር

1) ማመልከቻ የቀረበለት የምርመራ ቡድን ማመልከቻው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በሙሉ በአንድነት መሟላታቸውን በማረጋገጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ውሣኔ ይሰጣል፡፡

   ሀ/ አጓጓዡ እራሱ በማጓጓዣው ላይ በከፊልም ሆነ በሙሉ የባለቤትነት መብት ከሌለው፣

   ለ/ የማጓጓዣው ባለቤት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በወንጀሉ ተሳታፊ ወይም የወንጀሉ ፍሬ ተጠቃሚ ካልሆነ፣

   ሐ/ የተያዘው ማጓጓዣ የጉምሩክ ስነ ስርዓት የተፈፀመበት ከሆነ፣

   መ/ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም አግባብነት ባለው አካል ከተፈቀደው ውጪ በማጓጓዣው ላይ የሕገወጥ እቃ መደበቂያ ወይም ሻግ ያልተሰራለት ከሆነ፡፡

2) የምርመራ ቡድኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ በአንድነት ተሟልተው ካልተገኙ ተገቢውን ምርመራ በማካሄድ ለዐቃቤ ሕግ የሥራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

## 7. የገንዘብ ቅጣት አወሳሰን

1) በተያዘው ሕገ ወጥ እቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ፡-

ሀ/ እስከ ብር 50,000 የሆነ እንደሆነ ብር 10,000፣

ለ/ ከብር 50,001 እስከ 100,000 የሆነ እንደሆነ ብር 20,000

ሐ/ ከብር 100,001 እስከ 150,000 የሆነ እንደሆነ ብር 30,000

መ/ ከብር 150,001 እስከ 200,000 የሆነ እንደሆነ ብር 40,000

ሠ/ ከብር 200,000 በላይ የሆነ እንደሆነ ብር 50,000 ተቀጥቶ ማጓጓዣው ለባለቤቱ ይመለሳል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የተያዘው እቃ የተከለከለ ከሆነ ብር 50,000 በቁርጥ ተቀጥቶ ማጓጓዣው ይለቀቃል፡፡

3) የምርመራ ቡድኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰነውን የገንዘብ ቅጣት በመግለጽ ሰነዱን ለጉምሩክ ሥነ ስርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

## *8. ተደጋጋሚ ጥፋቶች*

በዚህ መመሪያ መሠረት ተቀጥቶ ማጓጓዣው የተለቀቀለት ባለቤት ማጓጓዣው በድጋሚ ሕገ ወጥ እቃ ጭኖ የተያዘ እንደሆነ ጉዳዩ ለሕግ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## *9. ሪፖርት ስለማቅረብ*

የምርመራ ቡድኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የተስተናገዱና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮችን መዝገብ ያደራጃል፤ በየወሩም ለመረጃ፣ ምርመራና ስጋት ሥራ አመራር እና ለዐቃቤ ሕግ የሥራ ሂደቶች ሪፖርት ይልካል፡፡

## *10. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተያዘ ማጓጓዣ ጉዳይ በዚህ መመሪያ መሠረት እልባት ያገኛል፡፡

## *11. <u>የተሻረ መመሪያ</u>*

የኮንትሮባንድ እቃዎችን በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎችን ለመወሰን በ1996 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## *12. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>*

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ------------------------ ቀን 2001 ዓ.ም**

*መላኩ ፈንታ*
*የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*
*ዋና ዳይሬክተር*